# የኦሪገን የስራ አጥነት መድን የጥቅማጥቅሞች ማመልከቻ

ይህ ቅጽ የFrances Online (frances.oregon.gov) እና የUI ሳምንታዊ የክፍያ መጠየቂያ ስልክ መስመር (UI Weekly Claim Line, 800-982-8920) አማራጭ ነው። Frances Online መጠቀም ወይም መደወል ካልቻሉ ብቻ ይህን ቅጽ ይጠቀሙ።

ይህ ቅጽ ለመደበኛ የስራ አጥ የመድን ዋስትና ብቁ መሆናቸውን ላረጋገጡ እና ሳምንታዊ ሪፖርታቸውን ማቅረብ ለሚፈልጉ ግለሰቦች የተዘጋጀ ነው። ሊያገኙ የሚችሉት የተረጋገጠ ክፍያ ከሌለዎት፣ በመጀመርያ ለመደበኛ የስራ አጥ የመድን ዋስትና ጥቅማ ጥቅም ማመልከቻ ማቅረብ አለብዎት።
ለመደበኛ የስራ አጥ የመድን ዋስትና ጥቅማ ጥቅም መጠየቅ ለሚፈልጉበት ለያንዳንዱ ሳምንት የሳምንት ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ይህን ቅጽ ይሙሉ።
ለያንዳንዱ ሳምንት የተለያየ ቅጽ መሙላት አለብዎት። እባክዎ በአሁኑ ወቅት በማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር በማህደር ላይ ያለውን ስምዎን ይጠቀሙ።

## የክፍያ ጠያቂ መረጃ

| መጠርያ ስም: | የአባት ስም: | የአያት ስም: |
|---|---|---|

የደንበኛ መታወቂያ ቁጥር ወይም የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር:

የሚከተሉት ጥያቄዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት የክፍያ ጥያቄ ለሚያቀርቡበት ሳምንት ብቻ ነው። በያንዳንዱ ሳምንት የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎችዎን ሪፖርት ማድረግ አለብዎት። በርትተው ስራ እየፈለጉ ነው ተብለው እንዲታሰቡ፣ የክፍያ ጥቅማ ጥቅም ለሚያቀርቡበት ለያንዳንዱ ሳምንት ቢያንስ አምስት የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎችን/ተግባራትን መፈጸም አለብዎት። ከሚያደርጓቸው የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱ በቀጥታ ከቀጣሪዎች ጋር የተደረጉ ግንኙነቶች መሆን አለባቸው። አሰሪዎ ለመጨረሻ ጊዜ ስራ ላይ ከነበሩበት ቀን ጀምሮ በአራት ሳምንታት ውስጥ ወደ ስራ ይመለሳሉ ብሎ የሚጠብቅ ከሆነ፣ ጊዜያዊ ስራ አጥ የሚለው ሳጥን ላይ ብቻ ምልክት ያድርጉ። አሰሪዎ ለመጨረሻ ጊዜ ስራ ላይ ከነበሩበት ቀን ጀምሮ በአራት ሳምንታት ውስጥ ወደ ስራ ይመለሳሉ ብሎ የማይጠብቅ ከሆነ እና እርስዎ በስህተት ጊዜያዊ ስራ አጥ የሚለው ሳጥን ላይ ምልክት ካደረጉ ክፍያዎን ሊያዘገይብዎ ይችላል። ሳምንታዊ የክፍያ ጥያቄዎን እንዴት ማቅረብ እንደሚችሉ ወይም ጊዜያዊ ስራ አጥ የሚለው ሳጥን ላይ መቼ ምልክት ማድረግ እንዳለብዎ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ Frances ውስጥ ያናግሩን።. ከኛ ጋር መገናኘት ስለሚችሉባቸው የተለያዩ መንገዶች የሚከተለው ድረገጽ ላይ ይማሩ/ይወቁ: unemployment.oregon.gov/am/contact-us

ክፍያ የተጠየቀበት ሳምንት (ከእሁድ ጀምሮ ቅዳሜ የሚያበቁ የሳምንቱ ቀናት):

## የተሰጡ የስራ ቅጥር ጥያቄዎች እና የስራ ስንብቶች

ባለፈው ሳምንት ውስጥ የቀረበልዎትን ማናቸውንም የስራ ቅጥር ጥያቄ ሳይቀበሉ ቀርተዋል? ☐ አዎ ☐ አይ

ባለፈው ሳምንት ስራ አቁመው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ

አዎ ካሉ፣ የአሰሪዎችን ስሞችና አድራሻዎች ይጻፉ:

ባለፈው ሳምንት ከስራ ተሰናብተው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ

አዎ ካሉ፣ የአሰሪዎችን ስሞችና አድራሻዎች ይጻፉ:

ባለፈው ሳምንት ከስራ ታግደው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ

አዎ ካሉ፣ የአሰሪዎችን ስሞችና አድራሻዎች ይጻፉ:

## መስራት መቻል እና ፈቃደኛ መሆን

ባለፈው ሳምንት ከቋሚ መኖርያዎ ውጪ ከሶስት ቀናት በላይ ቆይተው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ

ባለፈው ሳምንት ይፈልጉት የነበረውን ስራ ለመስራት በአካልም በአእምሮም ብቁ ነበሩ? ☐ አዎ ☐ አይ

ባለፈው ሳምንት በያንዳንዱ ቀን የሙሉ ሰዓት፣ የትርፍ ሰዓት እና ጊዜያዊ ስራ ለመስራት ፈቃደኛ እና ስራውን ለመቀበል እና ሪፖርት ለማድረግ ችሎታው ነበረዎት? ☐ አዎ ☐ አይ

## ስራ ፍለጋ

ባለፈው ሳምንት ስራ በንቃት እየፈለጉ ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ

ባለፈው ሳምንት ስራ ሰርተው ወይም ለሳምንቱ የእረፍት ክፍያ ተቀብለው ነበር ወይም ይቀበላሉ? ☐ አዎ ☐ አይ

ባለፈው ሳምንት ስራ ሰርተው ከነበረ፣ የሰሩባቸውን ሰዓታት ብዛት ያስገቡ (ወደሚቀርበው ሙሉ ሰዓት ያጠጋጉ):

ምንም እንኳን ክፍያው ባይከፈለዎትም፣ ከተቀናሽ በፊት የሚያገኙትን አጠቃላይ ገቢ ድምር (የክፍያ መጠን ከግብር በፊት) ያስገቡ: $

ከሰሩት ስራ ደመወዝ ተቀብለው ከሆነ፣ የአሰሪዎችን ስሞችና አድራሻዎች ይጻፉ:

ምንም እንኳን ክፍያው ባይከፈለዎትም፣ ከተቀናሾች በፊት ያለው የእረፍት፣ የፈቃድ ወይም ሌሎች ገቢዎችን መጠን ያስገቡ: $

የእረፍት፣ የፈቃድ ወይም ሌሎች ገቢዎች ክፍያ ተቀብለው ከሆነ፣ የአሰሪዎችን ስሞችና አድራሻዎች ይጻፉ:

## የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎች/ተግባራት

እባክዎ ባለፈው ሳምንት ስራ ፍለጋ ያናገሯቸውን ወይም የገኟቸውን አሰሪዎች ይመዝግቡ። በያንዳንዱ ሳምንት የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ ቢያንስ ሁለት አሰሪዎችን በቀጥታ ማናገር እና በድምሩ አምስት የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎች እና የስራ ግንኙነቶች ማድረግ አለብዎት። የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎችዎን ማቅረብ ወይም ስራ መፈለግ ካልቻሉ፣ ጥቅማ ጥቅምዎ ሊዘገይ ወይም ሊከለከል ይችላል። ከአሰሪ ጋር በቀጥታ መገናኘት ማለት ስለ ስራ መከፈቻ ለመጠየቅ ወይም አሰሪው በሚፈልገው መንገድ ለሚከፈት ስራ ለማመልከት ከአሰሪ ጋር በአካል፣ በስልክ፣ በፖስታ ወይም በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ መገናኘት ማለት ነው። የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎች በነዚህ ብቻ የተወሰኑ ባይሆኑም በWorkSource Oregon የስራ ምደባ አገልግሎቶች ለማግኘት መመዝገብን፣ በስራ ቅጥር መምሪያ ስፖንሰር የተደረጉ የስራ መደባ ስብሰባዎች ላይ መገኘትን፣ የስራ ምደባ ላይ የሚሰራ የስራ ክለብ ወይም የትስስር ቡድን ላይ መሳተፍን፣ አጠቃላይ የግል መረጃ ሰነድን ወይም ሲቪን ማሻሻልን፣ ለተለጠፈ ክፍት ስራ ምላሽ ሳይሰጡ ወይም ከአሰሪ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሳያደርጉ ጋዜጦችን ማገላበጥን ወይም የስራ ምደባ ድረገጾችን መጎብኘትን ያካትታል።

| በቀጥታ የተደረጉ ግንኙነቶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| የአሰሪ ስም | የስራ መደቡ መጠርያ | ቦታው | ግንኙነት የተደረገበት ቀን | ግንኙነት የተደረገበት ዘዴ (በአካል፣ በስልክ) | ውጤቶች (ተቀጠርኩ፣ አልተቀጠርኩም፣ አመልክቻለሁ) |
| | | | | | |
| | | | | | |

| ቀን | ሌሎች የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎች |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

| | |
|---|---|
| ☐ | እኔ በንግድ ስራዬ ላይ ከማህበሩ ስራ ውጪ የሆነ ስራ እንድፈልግ የማይፈቅድልኝ በጥሩ ሁኔታ ላይ የምገኝ የአንድ ማህበር አባል ነኝ። ከማህበሬ ጋር እየተገናኘሁ የቆየሁ ሲሆን ከስራ ውጪ ያሉ አባላት ዝርዝር ውስጥ ተመዝግቤያለሁ። ማህበሬ ከላከኝ ስራ የመቀበል እና ሪፖርት የማድረግ ችሎታው አለኝ። የሀሰት መልስ መስጠት ከተገቢው በላይ የሆነ ጥቅማ ጥቅም ክፍያ ሊያስከፍለኝ እና መልሼ ልከፍላቸው የሚገቡ ተጨማሪ ቅጣቶች ሊያስከትልብኝ የሚችል መሆኑን ተረድቻለሁ። |

የአንድ ማህበር አባል ነኝ ካሉ፣ የማህበርዎን ስምና ቁጥር ይጥቀሱ፡

| | |
|---|---|
| ☐ | እኔ ለጊዜው ስራ አጥ ነኝ ምክንያቱም ተቀንሻለሁ ወይም የስራ ሰዓቴ የተቀነሰ ሲሆን ከአሰሪዬ ጋር ተመልሼ እሰራለሁ ብዬ እጠብቃለሁ። ወደ ሙሉ ሰዓት ስራ ወይም ከሳምንታዊ ጥቅማ ጥቅሜ የበለጠ መጠን ክፍያ የሚያስገኝልኝ ስራ ወደ መስራት እመለሳለሁ። ጊዜያዌ ስራ አጥ በሆንኩበት ሳምንት እና ወደ ስራ በምመለስበት ሳምንት መካከል ያለው ጊዜ ከአራት (4) ሳምንታት የሚበልጥ አይደለም። ከአሰሪዬ ጋር እየተገናኘሁ ቆይቻለሁ። የሀሰት መልስ መስጠት ከተገቢው በላይ የሆነ ጥቅማ ጥቅም ክፍያ ሊያስከፍለኝ እና መልሼ ልከፍላቸው የሚገቡ ተጨማሪ ቅጣቶች ሊያስከትልብኝ የሚችል መሆኑን ተረድቻለሁ። |

ጊዜያዊ ስራ አጥ ነኝ ካሉ፣ ወደ ስራ እመለሳለሁ ብለው የሚጠብቁበትን ቀን ይጻፉ፡

## የክፍያ ጠያቂ ማረጋገጫ

የሰጠኋቸው መልሶች እኔ እስከማውቀው ድረስ እውነተኛ እና ትክክለኛ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ። ለሰጠኋቸው መልሶች ሃላፊነት አለብኝ። የሀሰት መልስ መስጠት መልሼ ልከፍለው የሚገባ ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅም ሊያስከትልብኝ ይችላል። ሃሰት ወይም አሳሳች መሆኑን እያወቅኩ መረጃ ከሰጠሁ ወይም መረጃ ሳልሰጥ ብቀር፣ እንደማጭበርበር የሚቆጠር እና በህግ የሚያስቀጣ መሆኑ ተድቻለሁ። ይህን ማረጋገጫ በህጉ መሰረት መስጠቴን እና የማይገባ ክፍያ ለማግኘት በማሰብ ሆነ ተብሎ የሚደረግ የተሳሳተ ትርጓሜ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑን ተረድቻለሁ።

☐ **ከላይ ባለው መግለጫ እስማማለሁ**

| **ፊርማ፡** | **ቀን፡** |
|---|---|

### እርዳታ ይፈልጋሉ?

ይህ መረጃ አስፈላጊ ነው። የኦሬጎን የቅጥር መምሪያ (The Oregon Employment Department, OED) የእኩል እድል ኤጀንሲ ነው። አገልግሎቶቻችንን መጠቀም እንዲችሉ OED ነፃ እገዛን ይሰጣል። አንዳንድ ምሳሌዎች የምልክት ቋንቋ እና የንግግር ቋንቋ አስተርጓሚዎች፣ በሌሎች ቋንቋዎች የተጻፉ ጽሑፎች፣ ትልቅ ህትመት፣ ኦዲዮ እና ሌሎች ቅርጸቶች ናቸው። እገዛ ለማግኘት፣ እባክዎ ወደ unemployment.oregon.gov/am ይሂዱ እና ያግኙን ቅጽ የሚለውን ጠቅ ያድርጉ ወይም በ 877-345-3484 ይደውሉልን። የTTY ተጠቃሚዎች 711 ይደውላሉ።

**እባክዎ የተሞላ ማመልከቻዎን በፖስታ ወይም በፋክስ ለሚከተለው ያስገቡ፡**
**በፖስታ:** Oregon Employment Department | P. O. Box 14135 | Salem, OR 97309-5068
**ፋክስ:** 866-345-1878